# ረሺድ ቤቡዶቭ ከ60 ዓመታት በፊት በአዲስ አበባ የተደረገለት የእንኳን ደህና መጣህ አቀባበል

ሙሳ ማርጃንለ
ዋና አዘጋጅ

ዘንድሮ አዘርባጃን የዲፕሎማቲክ አገልግሎት የጀመረችበትን አመት ታከብራለች፡፡ በጁላይ 09 ቀን 1919 የአዘርባጃን ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ግንኙነት መስክ ላይ ጊዜያዊ አዋጅ አውጥታ የነበረ ሲሆን ይህ አዋጅ በይፋ የሚታወቀው የመጀመሪያው ሕጋዊ ሰነድ ሲሆን ሰነዱ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት አካላትን ስልጣን በዝርዝር የያዘ ነበር፡፡ ይህ ቀን በአሁኑ ጊዜ የዲፕሎማቲክ ሰራተኞች የሙያ አመታዊ በዓል ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህ ጽሁፍ በአዘርባጃን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሆኑት ኤልማር ማማዲያሮፍ ለዚህ ቀን ተብሎ የተዘጋጀውን ንግግር የያዘ ነው፡፡

በዚህ ጽሁፍ በተጨማሪ የአዘርባጃን የሥነ-ጽሁፍ ሃያሲ ስለሆነው ራፋኤል ሁስዬኖቭ ማራኪ ጽሁፍ እናገኛለን፡፡ በዚህ ፅሁፍ ባለሙያው የ12ኛ ክፍለ ዘመን የአዘርባጃን ገጣሚ ስለነበረው እና እናቱ ኢትዮጵያዊ ስለነበረችው ሙጂራዲን ቤይላጋኒ ሕይወት እና ስራ የተረከበትን ስራ አካቷል፡፡ የታላቁ ካጋሊ ተማሪ የነበረውና ከኒዛሚ ጋንጃቪ በኋላ የተገኘው ታላቁ የሥነ-ጥበብ ሰው ሙጂራዲን በአዛርባጃን እና በአጠቀላይ በምስራቅ የሙስሊም ማሕበረሰብ ጥልቅ የሆነ የግጥም እና የቅኔ አሻራን አሳርፎ ያለፈ ሰው ነው፡፡ በተጨማሪም በ1959 የአዘርባጃን ሙዚቀኛ የነበረው ረሺድ ቤቡዶቭ ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱን እና ባቀረበውም ስራ ከፍተኛ ስኬት ተጎናጽፎ እንደነበረ ማውሳቱ ተገቢ ነው፡፡ ሙዚቀኛው አከናውኖት የነበረው የሙዚቃ ጉብኝት በአዘርባጃን እና በኢትዮጵያ መካከል የባህል ትስስር እንዲፈጠር መሰረት የጣለ ነበር፡፡

በተጨማሪም በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ባኩ በምትባለው የሶቭየት ከተማ ከዓመታት በፊት ትምህርታቸውን የተከታተሉ እና በቀሰሙትም ትምህርት በትውልድ ሀገራቸው ኃላፊነት ቦታን መያዝ የቻሉ ኢትዮጵያውያን የተመለከተ ጽሁፍ ተካቷል፡፡ እነዚህ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ባኩን የሚያስታውሷት ሞቅ ባለ ትዝታ ነው፡፡ ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ከቅርብ ጊዜ በፊት ባደረጉት የአዘርባጃን ጉብኝታቸው ያዩትን ሁኔታ የገለጹበት ውይይትም ዘና የሚያደርግ እና ትኩረትን የሚስብ ነው፡፡

ይህ ጽሁፍ በተጨማሪም የአዘርባጃንን ታሪካዊ እና የባህል ማዕከል የሆኑትን ሹሻ እና ሼኪን የተመለከተ ጽሁፍንም አካቷል፡፡